# የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን

ሰኔ 14፣ 2003 ዓም

## ኢሳት በቀጥታ ወደ  ኢትዮጵያ የሚያስተላልፈውን የፕሮግራም ሥርጭት መቋረጥ አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫ፣

ባለፈው ሰኔ 3 ቀን ከሁለት ወር በላይ በደረሰበት ከፍተኛ የዓየር ሞገድ የፕሮግራሙን ሥርጭት አቋርጦ የነበረው ኢሳት፣ በሰኔ 2/ 2003 ዓም በABS ሳተላይት ወደ መደበኛ ሥርጭቱ መመለሱን ለህዝብ ይፋ ማድረጋችን ይታወሳል። የኢትዮጵያ ህዝብ የኢሳትን ወደ ዓየር መመለስ የተቀበለው በከፍተኛ ደስታ እንደነበር ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የደረሱኑ በርካታ መልዕክቶች ያረጋግጣሉ።

ኢሳት ወደ ዓየር ተመልሶ ስርጭቱን በጀመረ በጥቂት ቀናት ውስጥ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለ ሐገሩም ሆነ ስለ ውጭው ዓለም በኢሳት በኩል የሚያገኘው ትክክለኛ መረጃ እንቅልፍ የነሳው በሥላጣን ላይ ያለው አካል፣ የሳተላይት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቱ ላይ በቻይና መንግስት በኩል ጫና በማሳደር አገልግሎቱን እንዲያቋርጥ በማድረግ፣ ኢሳትን ከዓየር ለማውረድ ችለዋል።

ውድ የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ በኢሳት ዙሪያ የተሰባሰብን ወገኖች ዛሬም እንደትላንቱ ይህ አስከፊ አፈና በምንም ዓይነት ማሸነፍ የለበትም የሚል ጽኑ እምነት አለን። ይህም በመሆኑ ኢሳትን ወደ ዓየር እንደገና ለመመለስ አስፈላጊውን ጥረት እያደረግን መሆኑን እና በቅርብ ጊዜም በቀጥታ ወደ ኢትዮጵያ ስርጭታችን እንደምንቀጥል ቃል እንገባለን።

ለነጻነት ለሙብት የምትቆረቆሩ ወገኖች፣ በዚህ ውጣ ውረድ በምንም ዓይነት ለአፈና መሸነፍ ስለማይኖርብን፣ በተለይ በውጭ ሀገር የምትኖሩ ኢትዮጵያዊያን ዛሬም እንደትላንትናው ለኢሳት የምታደርጉትን እርዳታ አጠናክራችሁ እንድትቀጥሉ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

የኢሳት የነጻነት መንፈስ ለዘላለም ይኑር!!!

ኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን፣
ሰኔ 2003 ዓ.ም

www.ethsat.com